# ብዕር ደህና ሰንብች!

(ለክቡር የኢትዮጵያ ባለቅኔ ለብላቴን ጌታ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን ስንብት)





... ቀለም እያጠጣ እሚያሸሞነሙንሽ ፣
ከልቡ አጠንበ ከኪሱ እማይለይሽ ፣
ሃቅ እያናገረ ባለም ያሳወቀሽ ፣
ቅኔ እያስተፋ ዕፁብ ድንቅ ያሰኘሽ፣
የዕድሜ ልክ ወዳጅሽ ክቡር ባልንጀራሽ ፣
ጸጋሽ አልፏልና ብዕር ምን ይዋጥሽ ? !

አምቦ ትምህርት ቤት በጠዋት «ለክፈሽው» ፣
... ኒዉዮርክ ከተማ ድረስ ያንንዝሽው፣
ሕይወቱን በሙሉ የኖርሽው አብረሽው፣
«እሣት ወይ አበባ... አበባ ወይ እሣት» ፣
ጥበብና እዉነት ... ቃጠሎ ወይ ውበት ፣
ሆነሽበት ኖረሽ ከእርሱ ሳትለዪ ፣
ጀግናሽ ጥሎሽ ሲሄድ እንግዲህ ምን ትዪ ? !

« ሀሁ በስድስት ወር » ፊደል አስቆጥሮ፣
«የከርሞ ሰው» «ሞረሽ» ... ታውኔት አስተምሮ፣
«እናት ዓለም ጠኑ» «የዋርካው ስር ምኞት» ... ፣
«ሀ ሁ ወይም ፐ ፑ» «ኦቴሎና ኀምሌት» ... ፣
ሲያፈስ የኖረብሽ ቋንቋውን ቀምሮ፣
ብዕር ደህና ሰንብች ! ሄደልሽ አምርሮ።





ውስጡውስጡን ጨምቆ የልቡን ትኩሳት፣
«ቴዎድሮስ» «... አባ ነፍሶ» «ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት» ...፣
የእማማ ኢትዮጵያን የእናት ሀገር ፍቅሩን፣
ሲገልፅ የኖረብሽ ወርቃማ ራዕዩን፣
ኮትኩቶ ያሳደገሽ ሌት-ተቀን ሳይሰለች፣
ጸጉ ጥሎሽ ሄዷል ብዕር ደህና ሰንብች!

ያንድነት ጠበቃ ያገር አድባር ዋርካ፣
ለሀገር ወዳዶች ሥሙ እሚያስመካ፣
ለኢትዮጵያ ታሪክ የኪነት አዝመራ፣
በተውኔት በቅኔ እስትንፋስ የዘራ፣
የጥንተ-ታሪክ ሊቅ የሥነ-ጽሑፍ አውራ፣
ዛሬስ ተሳቀቀ ከብዕሩ ጋራ።

የአፍሪቃን እናት የሰው ልጅ መሰረት፣
የኩሽ ዘር ከታቢ የቴአትር አባት፣
ቅኔ ለዛ አዋቂ የጥበብ ከሻኙ፣
ለእናት ሀገር ፍቅሩ ለሕዝቡ ታማኙ፣
የክፍለ-ዘመን ሰው አቻ ያልተገኘለት፣
ጀግናው ባለማዕረግ ባለቅኔው ሎሬት፣
ብላቴን ጌታችን ፣ ጸጋዬ ጸጋችን የሃቅ ተሟጋች፣
ትቶን አልፏልና ብዕር ደህና ሰንብች።

- ሎሬት ጸጋዬ !መልካም ሥምዎ፣ ታላቅ ሥራዎና ክቡር መንፈስዎ ዘወትር ከኢትዮጵያ ሀገራችንና ከእኛ ጋር ይኖራሉ።
  ሠላማዊ ዘልዓለማዊ እረፍት ይሁንልዎ!
- ለቤተሰብ፣ ለዘመድ-ለወዳጆችና ለአድናቂዎቻቸው ሁሉ መፅናናት ይሁን።

ከጌታቸው አበራ
(የካቲት 18 ቀን 1998 ዓ.ም)
ቴክሳስ - ዩናይትድ ስቴትስ